# ለመሆኑ ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ እንዴት እዚህ ደረሰች?

ከኃይለ ልዑል ግርማ

የቅንጅት ፓርቲ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር የሆነችው ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ የቅንጅት ፓርቲ አሸንፎ ሥልጣን ይዞ ቢሆን ኖሮ ሊኖራት የሚችለውን ሥልጣን ስመለከት እና ዛሬ የምትሰራውን ሥራ ሳገናዝነበው ከድንጋጤዬ የተነሳ ነጭ ላብ በጀርባዬ ይወርዳል:: አዎን ልታደርስ የምትችለውን ብሔራዊ ቀውስና ጥፋት በማሰብ ነው::

ለመሆኑ ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ ማናት? የሚለውን ጥያቄ ለማንሳት ያሳሰበኝ፤ በእርሷ መሪነት ቅንጅትን ፓርቲ የገባበትን ቀውስ ተቂቁማ፣ ሌሎች ኢትየጵያውያንን አስተባብራ ወያኔን ካለበት ለማውረድ ትችላለች ወይ ብዬ እራሴን ስጠይቅ የማገኘው መልስ እንኳንስ አገርን ለማዳንና ለመምራት ቀርቶ እራስዋ ከገባችበት ቀውስና ወጥመድ መውጣት አለመቻልዋን አስመስክራለች:: አሜሪካ ከመጣች በአንድ ወር ተኩል ውሰጥ ስንት ነገር ስትቀላምድና እረግርግ ውስጥ እንደገባችና እንደተያዘች አውሬ ስትዳክር ተመልከተናታል:: አዳምጠናታል::

አዎን ከሁለት ዓመት በፊት ቅንጅት ውሁድ ፓርቲ ሆነ ሲባልና ወጣት ሴት በፓርቲው ከፍተኛ እርከን ውስጥ መግባትዋ ሁላችንንም ተስፋ ያሰጠንና የተደሰትንበት ጉዳይ ነበር:: የቅንጅት መሪዎች ሲታሰሩ ከተደበቀችበት ኤምባሲ ወጥታ ከሌሎቹ ተደባለቀች ሲባል "ቆራጥ" "ጀግና" ተብላ ተሞግሳ ነበር:: ከእስር ቤትም ደብዳቤ ለአሜሪካ አምባሰደር ጻፈች ተብሎ አነበብን በጽሑፉ ይዘት ሁሉም ተደነቀ:: ግሩም ጽሑፍ ተብሎ ተወደሰችበት::

ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ብርቱካን እንዲህ አለች እየተባለ ተነገረ:: ዝናዋ ገነነ:: ለብርቱካን ግጥሙ ሙገሳው ተደረደረ:: ልዩ ቦታ ተሰጣት:: ብርቱካን ትፈታ ተብሎ በአደባባይ ተጮኸ:: ቲሸርቱ ሁሉ የብርቱካን ፎቶግራፍ ያለበት ሆነ:: ብርቱካን ብርቱካን ተባለ::

ከቃሊቲ እስር ቤት ሁሉም እንደወጡ ፕሬዚዳንቱ በመታመማቸው ምክንያት ስብሰባዎችን መምራት ጀመረች:: ብዙም አልቆየ ብርቱካን ማን እንደሆነች ትንሽ በትንሽ ታዬ:: መኪና የተሸለመች ጊዜ ወጥዋ እንዳማረላት ሴት ደስታዋ እራስዋን መልሶ ሊገድላት ነበር:: የፈረንሳይ ለጋሲዮን ደጉ ሕዝብ ከሌላው የአዲስ አበባ ሕዝብ ቀድሞ በመሸለሙ ዳገቱ ሁሉ ቁልቁለት ሆነ::

ብዙም አልቆየች በስብሰባ ላይ መቆጣትና አባላትን ማመናጨቅ ስትጀምር ነው ልጅቷ ምን ነካት ማለት የተጀመረው:: ይሁን እስቲ ኃላፊነት ከባድ ነው ተብሎ የከፋውም ሌላውም ቻል አደረገው::

ከሞትና ከአሜሪካ የሚቀር የለም ተብሎ አልነበር ያንን አባባል በተግባር ለመፈጸም ሩጫዋ ችኮላዋ ለጉድ ነበር:: ሕጻን ልጅዋን አሜሪካ ለማየት የተጣደፈች እናት ትመስል ነበር:: የናፈቃትን የአሜሪካንን ሕዝብ ለማየት በጣም ጓጓች:: አዎን ለምን ይሆን ያንቀዥቀዣት ያለም አይጠፋም:: አለቃዋ በዱባይ አድርጎ ቀደም ብሎ ስለመጣ ናፍቂት ይሆን? ያሰኛል::

ዋሽንግተን ዲሲ ገብታ ድፍን ሳምንት አልሆናትም ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የቅንጅት መሪ ናቸው ወይ ለተባለው ጥያቄ መልስ መመለስ ሲያቅታት:: ሳምንት አልሆናትም መሪያችሁን ትቀበላላችሁ ወይ ተብላ በተደጋጋሚ ለቀረበላት ጥያቄ አራምባና ቆቦ መልስ ስትሰጥ:: ለምን ይሆን ? የቦስተኑን ድራማ ከካሜራ ፊት ቆማ ስትሰራ የምትናገረው እና ፊትዋ የሚናገረው የተለያየ መሆኑን ለማየት ንግግርዋን አዳምጣችሁ መጨረስም አይኖርባችሁም::

እራስዋን እንዳልሆነች ያስታውቅ ነበር:: በየሄደችበት በተጠየቀችበት ሁሉ ውሸቱን ደጋገመችው:: በየስብሰባው ላይ የህሰትና ግራ የሚያጋባ መልስ መስጠቱን ተላመደችው::

አንድ በጣም የሚያስደስት ሆኖም ከውሸትዋ የተነሳ በጣም የሚያናድድ ነገር የተናገረችው በኮንግረስ አባሎች ፊት ኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ እስረኛ ቁጥር 100 ብቻ ነው ያለች ጊዜ ነው:: የሚያስደስተው ምነው እንደ አፍዋ ቢያደርገውና 100 የፖለቲካ እስረኛ ብቻ በኖረ ሲያሰኝ ሆኖም ግን በእርስዋ የፓርቲው ኃላፊነት ደረጃ ላይ ያለ ሰው ይህን አይነት የውሸት መልስ እንዴት ይሰጣል? የእርስዋ መለኪያ እንደወያኔ የተለየ ሆኖ ወደ መቶ ማውረድዋ ለወያኔ ማገዝዋ ከሆነም ብብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የታሰሩ እስረኞች ይፋረድዋት ብለን ማለፍ ነው:: አይቀርም ወይዘሮ ብርቱካን ይፋረዱዋታል:: የትግራይን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅዋ ያው ግልጽ ነው:: ወደ ካምፓቸው ለመግባት ማረጋገጥዋ ነው ብሎ ቢታለፍ ይቀላል:: በጣም አሳፋሪ የወያኔን የዘረኝነት በሽታ በልጅዋ አባት በኩል ተላልፎባት ይሆንም ያስብላል::

ለመሆኑ ወይዘሮ ብርቱካን እንዴት እዚህ ደረሰች?

የቀስተደመና አባል በሆነች አንድ ወር ባልሞላት ጊዜ ውስጥ እንዴት የቅንጅት ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነች ? የግንቦቱ 7 ቀን 1997 ዓ.ም ምርጫ ጊዜ የቅንጅት አባል አልነበረችም ታዲያ ከዚያ ምን ነበር የፖለቲካ አመለካከትዋና አቂምዋ ? ማነው ለምርጫ ያቀረባት ምን ነበር መመዘኛው? ሙያዋ ? ጾታዋ ? ወይስ የፖለቲካ ብስለቲና አመለካከትዋ? በእውነቱ ይሄ ሁሉ ሳይጣራ ለዚያ ደረጃ ያደረሳት ማነው? እንዴት ነው ባንድ ጊዜ ዝናዋ ሰማይ ጥግ የደረሰው? እስር ቤት ጻፈችው የተባለው ጽሑፍ እርሷ እንዳልጻፈችው ተረጋግጧል:: እድሜ ለአነ አንዳርጋቸው ጽጌ የፕሮፓጋንዳ ክፍል አይጥዋን ዝሆን እንቁራሪትዋን በሬ ማሳከል ይችላሉና የእነርሱ የወሬ ሰለባ ሆነን ብርቱካንን ሰማይ ጥግ ደረሰች:: በአለቃቸው ትእዛዝ በዶክተር ብርሃኑ ነጋ::

ሕዝብ የመረጣቸውን መሪዋን ገፍትራ ለመሄድ የሞከረች ሴትዮ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ትመራለች ብሎ ማሰብ ከየዋህነት ባሻገር የሚያስጠይቅም ነገር ነው:: የአለቃዋንና የፈጣሪዋን ዶክተር ብርሃኑን ፍላጎት ማሟላት ከሆነ ፍላጎትዋ በግሏ ማድረግ ትችላለች:: በሕዝብ ትግል ላይ ግን መቀለድ አትችልም:: የሕዝብም ድምጽ የሌላት ናትና የመለማመጃ ጊዜዋን ሳትጨርስ ካለችበት የኃላፊነት ቦታ በራስዋ እንድትለቅ አሊያም ፓርቲው ቀጥተኛ እርምጃ በመውሰድ ሊያሰናብታት ይገባል:: እርስዋን ለማዳን ሲሉ የሞቱቱን የሰፈርዋን ሰዎች እንኳን ከረሳች እና ገዳይ አስገዳዮቻቸውን ይቅርታ የምትጠይቅ ጋራ ጉዳይ የለንም:: ለሁሉም አገር ቤት ያለው ሕዝባችን በንዴት ተቃጥሎ እየጠበቃት ነው:: በተለይ "መኪና ሽለማት" የተባለው የፈረንሳይ ለጋሲዮን ሕዝብ:: ብርቱካን አበቃላት:: ገጣሚው እንዲህ ብሏል፤

"ብርቱካን ተክዬ እያልኩኝ ያፈራል
አይ አለማስተዋል ለካስ እምቧይ ኖርዋል"

እምቧይ ፈላጊ ፈልጋ ትሂድ:: ውሸታም በመሆንዋ አፈርኩባት::